የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 57
ADDIS ABABA, 11th July 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፮/፪ሺ፱ ዓ.ም
ለሁለተኛው የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለምዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………………………………ገፅ ፱ሺ፮፻፺፪

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፮/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለምዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሁለተኛው የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፪፻፴፮ ሚሊዮን ፬፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሁለት መቶ ሰላሣ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፩፻፳፭ ሚሊዮን አሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለምዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤-

**CONTENT**

PROCLAMATION NO.1026 /2017
International Development Association Financing Agreement for financing the Second Urban Water Supply and Sanitation Project Ratification Proclamation…………………………………page 9692

## PROCLAMATION No.1026/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 236,400,000 Special Drawing Rights (two hundred thirty six million four hundred thousand SDR) Regular Credit; and $125,000,000 (one hundred twenty five million United States Dollar) from Scale- Up Facility Credit for financing the Second Urban Water Supply and Sanitation Project was signed in Addis Ababa on the 7th day of April 2017;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 22th day of, June2017;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ “ለሁለተኛው የከተሞች የመጠጥ ውሃ እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፮/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>**የስምምነቱ መፅደቅ**</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረሙት የብድር ስምምነቶች ቁጥር 6007-ET (Regular Credit) እና 6008- ET (Scale Up Facility Credit) በዚህ አዋጅ ፀድቀዋል፡፡

፫. <u>**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፴፮ ሚሊዮን ፬፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሁለት መቶ ሰላሣ ስድስት ሚሊየን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ መደበኛ ብድር እና ከስኬል-አፕ ፋሲሊቲ ክሬዲት ፻፳፭ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር /አንድ መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “International Development Association Financing Agreement for Financing the Second Urban Water Supply and Sanitation Project Ratification Proclamation No. 1026/2017”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 6007-ET (Regular credit) and 6008-ET (Scale Up Facility Credit) signed in Addis Ababa on the 7th day of April 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 236, 400,000 Special Drawing Rights (two hundred thirty six million four hundred thousand SDR) Regular Credit; and $125,000,000 (one hundred twenty five million United States Dollar) Scale- Up Facility Credit in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 11th the day of July 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**